# የስድሳ ስድስት ነገር - አብዮት ወይስ ግርግር?

ታሪኩ አባዳማ ጥር 2003

ይህን አጭር ፅሁፍ በእንግሊዝኛ ጥቅስ መግቢያ በመክፈቴ ይቅርታ። ታሪክ ሲጠቀስ ከምንጩ ቢሆን የተሻለ ጥራት ይኖረዋል ከሚል ቀና አመለካከት የተነሳ መሆኑንም የተከበራችሁ አንባቢያን እንድትረዱልኝ በትህትና ጠይቃለሁ።

It was shortly past mid night, On 10 August 1792. The king had been sleeping fitfully after a pleasant meal. Suddenly an explosion shook him. Like a sleepwalker the king stumbled from his bed, a fat man in a dark-red dressing gown with his wig awry. His fat lips trembled. He was lost in the confusion of interrupted sleep and frightening noises.

'Louis, what is going on?' demanded the queen, clutching her nightgown anxiously around her. The tocsin kept on ringing.

The Duc de La Rochefoucauld charged into the room. The king looked startled: 'What is it? Une revolte?'
'Non, sire, c'est une revolution! It's the revolution!'[1]

ከ200 ዓመታት በፊት በፓሪስ ፈረንሳይ ስለተካሄደው አብዮት ሲተረክ የወቅቱ ንጉሥ ሉዪ16ኛ አብረው መነሳታቸው የተለመደ ነው። የፓሪስ ህዝብ ቁጣ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ቤተ-መንግስቱን ሲንጠው እንኳ ንጉሡ ገና ምን እየተካሄደ እንደሆነ በውል የተረዱ አይመስልም። ለንጉሥ ሉዪ16ኛ ሕዝባዊው አመፅ ማለት ሌላ ሳይሆን የከተማይቱ ድሆች የቀሰቀሱት ግርግር ነው። ድሆች በመኳንንቱ የቅንጦት ኑሮ ቀንተው በምቀኝነት የፈጠሩት አምባጓሮ ነው። ፈጣሪ ቀብቶ የሰጣቸውን ከአያት ቅድመ አያታቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ዙፋን ፣ የንጉሥነት ተፈጥሯዊ መብት በግርግር ለመንጠቅ የሚደረግ የመናጢዎች (little people) ሴራ ነው።

ንጉሥ ሉዪ16ኛ እልፍኝ አስከልካያቸውን 'ምንድነው ከውጪ የሚሰማው? ይኼ ግርግሩ ነው?' ብለው ሲጠይቁት 'የለም ጌታዬ ፣ ይሄ አብዮቱ ነው!' ብሎ መልስ ሰጥቷቸዋል። በዚህ የፈረንሳይ አብዮት ሂደት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች አልቀዋል። ከዘውድ ታማኞች እና አብዮተኞች ጭምር በጥቂት ቀናት ብቻ የፓሪስን ጎዳናዎች በሙታን ያጥለቀለቀ ሽዎች የወደቁበት እልቂት ደርሷል። ንጉሱ እና ቤተሰባቸው ፣ ባለሥልጣኖቻቸው ጭምር በስለታም ጎራዴ guillotin አንገታቸው በአደባባይ ሲቀላ ኳስ ጎል ሲገባ እንደሚሆነው አይነት ህዝቡ በደስታ ጨኸት ያስተጋባ ነበር።

ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት ፈረንሳይ ላይ የታየው አይነት አብዮት እስከ አሁን ዘመን ድረስ በየገሩ መካሄዱን ታሪክም በኛ ዕድሜ ካየነውም መመስከር እንችላለን። በሀያኛው ክፍለ ዘመን እንኳ ንጉሶች እንደ ሩሲያ ፣ ኢራን ፣ ሀይቲ ፣ ሊቢያ ፣ ግብፅ፣ አፍጋኒስታን እናም እኛ አገር ኢትዮጵያ ከዙፋናቸው እየተዘረጠጡ ገሚሱ አገር ለቀው ሲሸሹ ጥቂቱ ደግሞ የአብዮተኞች ሰይፍ ሰለባ ሆነዋል። ከራሳችን ታሪክ እንደምንገነዘበው የ66ቱ አብዮት በብዙሀን ዜጎች ንቁ ተሳትፎ ተካሂዷል። አብዮት የተባለውም ለዚህ ነበር።

እስከ 66 ዋዜማ እና አጥቢያ ድረስ ፍትሀዊ አገዛዝ እንዲመጣ 'ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም' እያለ ጥሪ ሲያደርግ የነበረው የተማረ ሀይል ሳይቀር በማርክሲዝም ሌኒንዚም መርህ 'የወዛደር/ላብአደር እና አርሶ አደር ትብብር' ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ባስቸኳይ እንዲመሠረት ጥሪውን በየቡድን ማስተጋባቱን እናስታውሳለን። ወጣቶች በጥናት ቡድን እና በህዋስ ተደራጅተው የወዘደር/ላብ አደር አምባገነንነት (The dictatorship of the proletarian) በ'ሣይንሳዊ' ንድፈ ሀሰብ ላይ ተገንብቶ እውን የሚሆንበትን መላ በማጥናት ሥራ ላይ መጠመዳቸውም እውነት ነበር።

ፈላጭ ቆራጭ መንግስት እንዲመጣ ተራማጁ ሁሉ ከቀያይ መፃህፍት ጥቅሶችን አስረጂ እያቀረበ ፣ ቻይና ፣ ቬትናም ፣ ኩባ ብሎ ታሪክ እያጣቀሰ ያብዮቱ አቅጣጭ ምን መሆን እንዳለበት በማያሻማ ቁርጠኝነት ማመልከቱም እውነት ነበር። በዚህ አይነት ቀስ በቀስ ድርጅታዊ ቅርፅ እየያዘ የመጣው ትግል በወታደሮች ግትር የሥልጣን ቅሚያ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ በቀላሉ የማይተመን ሰብአዊ እና ቁሳዊ ውድመት ደርሷል። ብዙሀኑ ህዝብ በጭቆና እና በድህነት ቀንበር ሥር የተንገላታ እንደመሆኑ ይህንን የጭቁኖች ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ለማየት ያለውን ጉጉት በተለያየ መልኩ ድጋፍ በማድረግ እና ልዩ ትኩረት በመስጠት አግዟል።

የስድሳ ስድስቱን ህዝባዊ አብዮት ማቆም ይቻል ነበር? ካልተቻለስ እየተከተለ የነበረውን ግራ ዝናባሌ በሌላ ቀይሶ እንዲቀጥል ማድረግ ይቻል ነበር? ይህን ጥያቄ በዚያን ዘመን ለመመለስ እና አብዮቱን ለመግታት ብሎም

[1] Blood of Revolution pages 11,12. Erik Durschmied

አቅጣጫውን ለመቀየር የሞከሩ ጥቂት አልነበሩም - ይሁንና የአብዮቱ ሂደት ከማንም መልካም ፈቃድ እና ቁጥጥር ውጭ ሆኖ ንጉሡ እንደ ቀድሞው መግዛት ተስኗቸው አይወድቁ አወዳደቅ ገጥሟቸዋል።

የሕዝብ ብሶት በቸልታ እና በአፈና ሲታመቅ እንደ ተዳፈነ እሳተ ገሞራ ቀን ቆጥሮ መገንፈሉ የማይቀር ነው። ሲገነፍል ደግሞ የሚከተለው ህግ የለም - ግብታዊ ነው ፣ በቁጣ ፣ ጥላቻ እና እልህ የታጨቀ ስሜት ነው። በዚህ የተነሳ አብዮቱ እጅግ አደገኛ የሆኑ ሰዎች እጅ ሊወድቅ እንደሚችል እንኳ ለግዜው የሚያስብ የለም። እኔ ካልገዛሁ ያሻው ይሁን በሚል ሀላፊነት የጎደለው አመለካከት ገገርዎች ተገደው ከሥልጣናቸው እስኪወገዱ የመጨረሻ ሰዓት ድረስ ቤተ-መንግስት መኮፈስን መርጠዋል። በ66 የሆነው ይህ ነበር - ነገ የሚሆነውም ይኸው ነው።

ንጉሳዊው አገዛዝ ፍፁማዊ ስለነበር ምንም አይነት የፖሊቲካ ፓርቲ ባገሪቱ እንዲኖር አልፈቀደም። ከንጉሡ በስተቀር ማንም የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ሊመኝ ወይም ሊቀናቀን እንዳይችል አፈናው በሕግ ጠብቋል። በዚህ ሁኔታ አንድ አይነት ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ቢከሰት እንኳ እንደ ማስታገሻ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ድርጅት ወይም አማራጭ ፓርቲ አልነበረም።

እንደ ንጉሡ እና መኳንንቱ ከሆነ ያለው ንጉሥ አንድ እና አንድ ብቻ ነው - እሱም ዘላለማዊ ነው። ንጉሥ ይሙት ካላችሁ የመጣውን መቀበል ነው የሚል ብቸኛ ምርጫ ትተውልናል። ንጉሡ ከወደቀ አገርም አብሮ ቢወድቅ ደንታ ያልነበራቸው ጭፍን መኳንንት የነገሱበት ዘመን ነበር። እውን የፖለቲካ ፓርቲ ባህል ተፈቅዶ ቆይቶ ቢሆን ኖሮ ደርግ የሚባል ነገር ይመሰረት ነበር? ደርግ እራሱ 'ስልጣን ላይ የወጣሁት ሌላ የተደራጀ የፖለቲካ ፓርቲ የሌለ በመሆኑ ነው' በማለት ደጋግሞ ሲገልፅ ሰምተናል። ሁሉም አምባገነን ሥልጣን የያዝኩት በሕዝብ ፈቃድ ነው እንደሚለው አይነት መሆኑ ነው። ይሁንና ሥልጣን ላይ መውጣቱንስ ወጣህ ታዲያ እዚያው ሙጥኝ ብለህ መቅረትህ ምን የሚሉት ነው ለሚለው ጥያቄ ደርግ አጥጋቢ መልስ የለውም። ያበቃለት ዘውዳዊ ሥርዓት በምን ይተካ ለሚለው መልስ በግዜው ከደርግ ሌላ ምን አማራጭ ነበረ? እናም አብዮቱ በወታደር ቁጥጥር ስር ዋለ - ሥልጣን ለወታደር አደራ ሰጥቶ በጤና ይመለሳል ማለት ዘበት ሆነ።

ለዚህ ፅሁፍ አቅራቢ የደርግ ትልቁ ወንጀል የህዝብ አብዮት ፣ የህዝብ ራዕይ ነጥቀ በእጁ መናኛ ያስከተለው ጥፋት ይመስለኛል - እናም ዳኝነቱ የዚያ አብዮት ባለቤት ለሆነው ብዙሀን ዜጋ መተው ያለበት መሆኑን በፅናት ያምናል። የተጎዱ ፣ የተቀሙ ቤተሰቦች ጉዳይ ተደርጎ እጅግ ውሱን በሆነ ክልል ማስቀመጡ አብዮቱ እንዳልነበረ መካድ ነው።

አብዮቱ ወደ ጠየቀው አምባገነን የጭቁኖች መንግስት ጉዳይ እንመለስ። በወቅቱ እንደሚታወሰው ጠላቶቻችን ሶስት መሆናቸውን ሁሉም ፖለቲከኞች ነገሩን - ፊውዳሊዝም ፣ ካፒታሊዝም እና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም። ፈላጭ ቆራጭነት በነኝህ ሶስት ጠላቶች መቃብር ላይ እንዲረጋገጥ ተራማጆች ባንድነትም በተናጠልም ጥሪ አደረጉ። የተራማጅ ሀይሎችን መፈክር በመጋራት ደርግ እኔም ከጭቁኑ አብራክ የተገኘሁ ዜጋ ነኝ አለ - አብዮቱ ያነሳቸውን ጥያቄዎች እንደ ማንኛውም ጭቁን ማስተናገድ እንደሚችልም አወጀ። በዚህ ረገድ ጎልቶ ይታይ የነበረው ጥያቄ 'ሃቀኛውን' ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ለመመስረት ከኔ የተሻለ ብቃት ያለው የለም በሚል በተራማጅ ድርጅቶች መካከል የነበረው ፉክክር ብቻ ነበር። ደርግም የፉክክሩ አካል በመሆን ያምባገነን አገዛዝ ሽምቀቆውን እያጠበቀ ሄደ።

አንዱ ሌላውን በራኘር ፣ ከላሽ ፣ ቀልባሽ ፣ ርዝራዥ፣ አደናጋሪ ብሎ ከመክሰስ በስተቀር ፈላጭ ቆራጭ መንግስት በማምጣቱ ጥያቄ ላይ መሠረታዊ ፀብ አልነበረም። ቤተ-መንግሥቱን የ'ጭቁኖች' ፈላጭ ቆራጭ መንግስት አምባ ለማድረግ የተደራጀ ፖለቲከኛ ሁሉ ይሆናል ብሎ ባመነበት መንገድ ትግሉን ፣ ጥረቱን ፣ ሴራውን እና ብልሀቱን መጠቀም ያዘ።

ስድሳ ስድስት አጥቢያ ካለምንም 'ሳይንሳዊ' ትንታኔ ሲቃኝ ይህን ይመስል ነበር። ድራማው ቀጠለ - ደርግ ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ለማምጣት ያለውን ቁርጠኝነት ለሁሉም ወገን ለማረጋገጥ ሲል በጭቁኑ ህዝብ ስም አህዱ ብሎ የ'ፊውዶ-ቡርዧውን' ባለስልጣናት ሰብአዊነት በጎደለው አግባብ በመረሸን 'ተራማጅ' እርምጃ በ'አድህሪያን' ላይ ወሰደ። ደርግ በዚህ ክፉ አጋጣሚ ለፈላጭ ቆራጭነት በብቃት መዘጋጀቱን አመለከተ። ፈላጭ ቆራጭ መሆን ከዚህ ሌላ ትርጉም እንደሌለው ለማረጋገጥ ከሌሎች ፖለቲካ ሀይሎች የተለየ ዕድል ያገኘ መስሎት ፉክክሩን በአንደኝነት በማጠናቀቅ ደርግ በዘመኑ 'አብዮታዊ' ኩራት እና ትምክህት አደረበት።

መስከረም 2 ቀን 1967 ዓም ከአብዮት ወደ ፍፁም አምባገነንነት እና ሥርዓት የለሽ ዘመን ሽግግር የተደረገ መሆኑን በወቅቱ በውል የተገነዘቡ የአብዮቱ ወገኖች ነበሩ ማለት በጣም ያስቸግራል።
ኢትዮጵያ ውስጥ በየካቲት ስድሳ ስድስት አመተ ምህረት ህዝቡ ሆ ብሎ ሥር ነቀል ለውጥ እንዲደረግ አምርሮ የጠየቀው በፓርቲ አደረጅነት ወይም አመራር አልነበረም። የተማሪ ረብሻ ፣ የገበሬ ግርግር እየተባለ ካንዱ ዘመን

ወደሚቀጥለው እየከረረ የመጣው ግብግብ ወደ መምህሩ ፣ ታክሲ ነጂው - እስላሙ ክርስቲያኑ ተሸጋግሮ ያዬውን አገዛዝ ጭንቅ ውስጥ ከመክተት አልፎ ማንበርከክ ችሏል።

ስልጣን በዕድሜ ከጃጁት ንጉስ የነጠቁት የደርግ አባል ወታደሮች ሳይቀሩ የነግ ተነገ ወዲያ እጣ ፈንታቸው ምን እንደሆነ በውል አያውቁም። ከወታደር ኑሮ ወደ ቤተ መንግስት ከዚያም ወደ ዘብጥያ የሚወስደውን ረጅም የጥፋት ጎዳና እንደተያያዙት ጨርሶ አልተገነዘቡም። ብቻ አንዴ ስልጣን ላይ ከወጡ ተመልሰው የማይወርዱበትን ብልሀት በመፍጠር ግዳጅ ላይ ተጠመዱ። የስልጣን ዘመናቸው የሚረዝምበትን እናም ሌላው የፖለቲካ ሀይል ሁሉ የሚኮላሽበትን እርምጃ ሲወስዱ ፤ ለሁሉም ችግር ወታደራዊ መፍትሄ ሲሰጡ ሳይነጋ መሸባቸው።

ለፈላጭ ቆራጩ መንግስት መምጣት እውን መሆን ዋስትና ለመስጠት ሲባል ስድሳ ምናምን ኢትዮጵያውያን ካለ ፍርድ ሞቱ። ሞት ግን እዚያ አላቆመም። ባንዳ እዚህ አናርኪስት እዚያ ፣ አድሀሪ እዚህ ቀልባሽ እዚያ እየተባለ አብዮተኛ ሁሉ 'ለሃቀኛው' የወዛደር/ላብአደር ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ምስረታ በቀናኢነት ተሰልፎ ተገዳደለ።

ደርግ ፣ አብዮት እና የፈላጭ ቆራጭነት ምኞት ነገሱ። በከተማ ገጠሩ ግርግር እየተባባሰ ፣ ዘፈቀደ ግድያ ሥር እየሰደደ መጣ። በነፃ መደራጀት ፣ ተቃውሞ ሰልፍ መጥራት ፣ ሥራ ማቆም አድማ መምታት ፀረ-አብዮት መሆኑ ታወጀ። አምባገነንነት በምንም መልኩ ይሁን በማንም ይመራ የመጨረሻው ውጤት ይኸው ነው። የአምባገነን መንግስት እንዲመጣ መታገል ለዚህ አይነቱ መጨረሻ ሊዳርግ እንደሚችል የተገነዘበ ማን ነበር?

ስድሳ ስድስት የተነሳውን ጥያቄ እና የሆነውን ዛሬ ካለንበት አዲስ ዘመን እና አዲስ መንፈስ አንፃር ለመመርመር የሚሹ እንዳሉ ሁሉ ያለፈው ሁኔታ በራሱ ተጨባጭ አገራዊ እና አለም አቀፋዊ ሁኔታ ሊዳኝ ይገበዋል የሚሉ አልጠፉም። ይሁንና ዛሬ ሁሉም እንደሚገነዘበው ስድሳ ስድስት እንደ ግርግር - የተከተለው ጥፋት እንደ ተራ ወንጀል ተፈርጇል። ማንኛውም ተራ ወንጀል - አድራጊ ፣ ተባባሪ ፣ ወንጀሉ እንዲፈፀም በቃላት እና ድርጊት ያበረታታ ፣ ወንጀሉ ሲፈፀም በቸልታ ያለፈ እያለ ብዙ ዘርፍ ያለው የመቅጫ አንቀፆች አሉት። አብዮቱ እንደ ግርግር ፣ የተከተለው ጥፋት ወንጀል ከሆነ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የፖሊስ መጥሪያ መታተም ይኖርበታል። 'ንጉሱ ይሰቀል ፣ አስራችሁ አትቀልቡ' ካልነው ጀምሮ 'ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት ይመሥረት' ብሎ እስከታገለው የግዜው ተራማጅ ድረስ ተጠያቂ መሆን እንዳለባቸው ቢያንስ ለህሊናችን እናረጋግጥ።

በአብዮት ዘመን የተፈፀሙ ኢሰብአዊ አድራጎቶችን መርምሮ እውነቱን ለቋሚው እና ለመጭው ትውልድ ትምህርት እንዲሆን የመመዝገቡ ድርሻ የታሪክ ፀሀፊዎች ነው። እኛ የምንመሰክረው ግን የትም ይሁን የት አብዮት በማይፈፀም ባዶ ተስፋ ሰክሮ በጭፍን እርምጃ ደም የሚፈስበት ማህበራዊ ክስተት መሆኑን ብቻ ነው። ይህ የሆነው ደግሞ እኛ አገር ብቻ አይደለም - የኛን አገር አዲስ እና ልዩ የሚያደርገው ያካሄድነውን አብዮት እንደ ወንጀል ለመቁጠር ካላንዳች ይሉኝታ መነሳታችን ብቻ ነው። የትናንቱን አብዮት ክደን ሌላ አብየት እንዲመጣ መመኘት ይቻል ይሆን?

የአብዮቱ ሰለባ የሆኑ መኳንንት እና መሳፍንት ልጆች ሳይቀሩ ዛሬ ያንን አብዮት ግርግር መሆኑን እና ወንጀል መፈፀሙን የህግ አንቀፅ እየጠቀሱ ትንተና ማድረግ ይዘዋል። መልካም ነው። ግን የማስታውሳቸው አንድ ነገር ቢኖር በፈረንሳይ አብዮት ሂደት የንጉሱ ወንድም ልጅ እና የቅርብ አማካሪ ሚራቦ (Mirabeau Duc de Orleans) በጠና ታሞ ከመሞቱ በፊት ንጉሡን በድፍረት ቀርቦ፡- "I leave you with a hopeless and cruel thought. Unless you stop the excess, they will lead on to tragedy, from single murder to massacre, from the fall of a king to the fall a country" የኛ ነገሥታት እና መኳንንት በሌሎች ነገሥታት እና መኳንንት ላይ ስለደረሰው ክፉ እና ደግ ታሪክ ለማወቅ ከተራው ሰው የተሻለ ዕድል ነበራቸው። ትናንት ተምረው አላየናቸውም - ዛሬም ከታሪክ የተማሩ አይመስልም።

በመጨረሻም ፣ የፈረንሳዩ ንጉስ ሉዪ16ኛ ፓሪስ በአብዮታዊ ማዕበል ስትናጥ እና ሥልጣናቸው እያበቃ መሆኑን ሲረዱ አማካሪዎቻቸውን ሰብስበው 'ለመሆኑ አብዮት እንዳይኖር ማድረግ አይቻልም? (Was revolution unavoidable?)' ብለው ለሰነዘሩት ጥያቄ ያገኙት የማያወላዳ መልስ 'You brought it on yourself' በቀላል አማርኛ ሲተረጎም 'የዘራኸውን ታጭዳለህ' የሚል ነበር።

የአፄ ሀይለሥላሴ ዘውዳዊ አገዛዝ የተገረሰሰው እራሱ አምጦ በወለደው አብዮት ነበር። አብዮት ደግሞ አዲስ እና ብሩህ ተስፋ በሚታያቸው እንግልት ዜጎች ሙሉ ተሳትፎ የሚከናወን የብሶት መግለጫ ፣ የመፍትሄ ማፈላለጊያ ክስተት ነው ፤ እናም አብዮት በማንም መልካም ፈቃድ የሚካሄድ ጉዳይ አይደለም - ሁልግዜም ግብታዊ ነው።

ጨቋኝ ገዢዎችን እስከ አከርካሪያቸው ዘልቆ የሰባበረው የስድሳ ስድስት አብዮት ለዘላለም ይኑር!!